# በአዲሱ ዓመት የሚያስፈልገን የተቃውሞ ፖለቲካ ህዳሴ ነው!!

# (ክፍል 2)

“የፖለቲካ ለውጥ ያስፈልገናል” በሚል የቀረበውን የአዲስ ጉዳይ መጽሄት ትርክት በመንተራስ ይልቁንስ የሚያስፈልገን የተቃውሞው ፖለቲካ ህዳሤ እንደሆነ ያብራራሁበትን የመጀመሪያ ክፍል መጣጥፍ ስደመድም በሁለተኛው ክፍል በዚሁ ርዕሠ ጉዳይ እና “ኢትዮጵያ በአዲሱ ዓመት ምኞትና ተስፋ” በሚል የቀረበውን የተቃዋሚ ሃይሎች የተለመደ ኡኡታ የምናይ መሆኑን አስታውሼ ነበር፡፡ ስለሆነም ወደተቃዋሚዎቹ ምኞትና ተስፋ ምዘናችን እናምራ፡፡

በነገራችን ላይ በዚህ ምኞትና ተስፋን በተመለከተው ትርክት አስተያየት የሰጡት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች የመድረኩ አቶ ቡልቻ ደመቅሣ፣ የአንድነቱ አቶ አሥራት ጣሤና የሠማያዊው ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት ሲሆኑ ከምሁራኑም ወገን ዶ/ር ዳኛቸው አሠፋም ያሉ መሆኑንም መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን የዶ/ር ዳኛቸው ተስፋና ምኞት ከተቃዋሚዎቹ በይዘት የተለየ፤ ቅንነት የተሞላውና በርግጥም ተቃዋሚዎቹ ህዳሤ የሚያሻቸው መሆኑን የሚጠቁም በመሆኑ በጽሁፌ ማሣረጊያ እንደ መደምደሚያም እንደ ምኞትና ተስፋም ብጠቀመው የተሻለ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ስለሆነም ጉዳያችንን ከአቶ ቡልቻ ደመቅሣ ስንጀምር ያለፈው ዓመት ሃገራችን ወደፊት የገሠገሠችበት ሳይሆን ወደኋላ የቀረችበት መስሎ እንደተሰማቸው ያወሡት አቶ ቡልቻ ብርሃን እንደማይታያቸውና ተስፋ ማጣታቸውንም ገልፀዋል፡፡ በዚህ ምኞትና ተስፋ ያላበቁት አቶ ቡልቻ እንደ ፖለቲከኛ ሣይሆን በተለመደው የፖለቲካ ሽፋን እንደ ነጋዴም የሰጡት አስተያየት አለ፡፡ ለምሳሌ ሲሉ ነጋዴያዊ አስተያየታቸውን የጀመሩት አቶ ቡልቻ ለምሳሌ "ከቻይና ለሚመጣ ዕቃ በሙሉ ክፍያው የሚከናወነው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ብቻ ነው፡፡ የግል ባንኮች በጭራሽ ከቻይና ዕቃ በማስመጣት ሥራ መሣተፍ አይችሉም፡፡ በዚህም የመንግስት እጅ በጣም መርዘሙን እና የማይነካው ነገር እንደሌለ ማረጋገጥ ይቻለናል" ብለዋል፡፡

ሌላውና አስገራሚው የአቶ ቡልቻ አስተያየት ደግሞ "ተቃዋሚዎች እየደከሙ አልሄዱም ያቃታቸው ማደግ ነው" በማለት ለዚህም ኢህአዴግን ተጠያቂ ማድረጋቸው እና በወጣቱ የነቃ ተሣትፎ ፖለቲካው እንደሚለወጥም ያላቸውን ተስፋ መግለጣቸው ነው፡፡

የአንድነቱ አቶ አስራት ጣሤም በተመሣሣይ ኢህአዴግን "ችግሮችን በሠከነ አእምሮ በሠጥቶ መቀበል ስልት መፍታት የተሣነው" ፓርቲ ሢሉ ከዘረጠጡት በኋላ ተስፋቸውና ምኞታቸው “የሚሊዮኖች ድምጽ ለነፃነት” መሆኑን በመጥቀስ ተመፃድቀዋል፡፡

የተለመደውን የከሠረ ፖለቲካ መሠረት በማድረግ ከሃይማኖቶች ለማትረፍ የሚጥሩት ሠማያዊው ኢንጂነር ይልቃልም ኢህአዴግን በመሸርደድ አስተያየታቸውን የጀመሩት በሙስሊሙ ማህበረሠብ ስም ለሚንቀሣቀሱ ሃይሎች ጥብቅና በመቆም ነው፡፡ ሌላውና ለፖለቲካ ትርፍ አገልግሎት ላይ የዋለውም የዜጎች መፈናቀል ለሠማያዊው ሠው ዝርጠጣ በምክንያትነት ቀርቧል፡፡ ከዚያም የኢትዮጵያ ህዝብ የለውጥ ፍላጎት ማሣየቱ ተስፋዬ ነው በማት በአክራሪ ኃይሎች የተጠለፈውን የሠማያዊ ፓርቲ ሠልፍ ሊመፃደቁበት ሞክረዋል፡፡

እጅጉን የሚገርመው ግን ያለፈውን ዓመት "በተፎካካሪ ፓርቲዎች አካባቢ መናበብና ወደውጤት የመሄድ መንገድ የተጀመረበት ዓመት ነበር" ሚሉ ሰማያዊው የሠጡት አስተያየት ነው፡፡

ከዚህ አስተያየት በመነሣት ነው እንግዲህ ተቃዋሚው ፖለቲካ ህዳሜ ያሻዋል የምለው፡፡ ለምን ቢሉ ከላይ የተጠቀሱት ትርክቶች የጨለምተኝነት መገለጫ እንጂ የሥርዓቱ አለመሆናቸውን የሚያሣዩና ባለፈው ዓመት የተሠሩ በርካታ የልማት እና የዴሞክራሣያዊ ሥርዓት ግንባታ ክንውኖች በመኖራቸው ነው፡፡

ተሃድሦ ያሻቸዋል የምላቸው የተቃውሞው ፖለቲካ መስመርተኞች ብዙ ጊዜ ሥርዓቱን ሊያወግዙና ሊሸረድዱ ሲፈልጉ ስለዴሞክራሲዊ ሥርዓትና ስለመልካም አስተዳደር አብዝተው ያነሣሉ፡፡

በዚህ ዘርፍ ችግር እንኳ ቢኖር ጠንካራ ጎኑን አለማንሣታቸው ሳያንሥ ስለልማቱና በዓይናችን ስለምናያቸው የመሠረተ ልማት ግንባታዎች "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" ብለው ማለፋቸው ግን ያሣዝናልም፣ ያሣፍራልም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ የወላድ መካን መሆኗን ስለሚያረጋግጥ ተሃድሷቸውን ብንመኝ የሚገርም አይሆንም፡፡

ለማንኛውም ወደሚያሳዝኑበት ዴሞክራሲንና መልካም አስተዳደሩን ወደተመለከቱት ነጥቦች ስንሻገር በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን እና መልካም አስተዳደርን የመገንባትና የማስፈን መነሻዎች በህገ መንግስቱ ላይ የሠፈሩ የዴሞክራሲ መርሆዎች መሆናቸው ላይ አስምረን መሆን ይኖርብናል፡
፡

የዴሞክራሲ ባህልን ለመገንባት ባጠቃላይ የተማረና አቅም ያለው ዜጋ ማፍራት መሠረት መሆኑን በመገንዘብ ከሥነ ዜጋ ትምህርት ማስፋፋትና ጥራቱን ከማረጋገጥ ጀምሮ ወጣቱ ዴሞክራሲያዊ ባህሉ እንዲያድግ የሚያግዙ ተቋማት ባለፈው ዓመት በስፋት ተፈጥረዋል፡፡ በዚህም በብሄረሠቦች፣ በፆታዎች፣ በሃይማኖት እኩልነት ላይ የተሻለና የተስተካከለ አመለካከት ማሣደር የተቻለበትም አመት እንደነበር መታወስ ይገባዋል፡፤

ዴሞክራሲያዊነትን የሚፈጽሙና የሚያስፈፅሙ ተቋማት በተለይ ከአዲስ አበባና የአካባቢ ምክር ቤት ምርጫ ጋር በተያያዘ የተስተካከለና የሠከነ አመለካከት ላይ ተመስርተው ይህንኑ ለማጎልበት የሚተጉ እንዲሆኑ ብዙ ጥረት የተደረገበትና ውጤትም የተገኘበት ዓመት እንደነበርም መዘንጋት አይገባም፡፡

ለተቃዋሚ ፓርቲዎች አለማደግ ምክንያት ነው ሲሉ አቶ ቡልቻ የሸረደዱት ኢህአዴግ ባሳለፍነው ዓመት በተለይም ከላይ እንደተመለከተው ከአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ ጋር በተያያዘ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተስተካከለና በሠከነ መንገድ የሚንቀሣቀሡበትን ምህዳር በማስፋትና እነርሡንም ለማብቃት ያደረገው ሠፊ ጥረት በራሣቸው ትናንሽ ቢሮ ውስጥ በሚደረጉ ትልልቅ ሽኩቻዎች የከሸፉ ከመሆናቸው አንፃር መታሠብ የሚገባው ሢሆን የኢትዮጵያን ፖለቲካ በተመለከተም “ነገሩ ሁሉ ከላይ ወደታች ነገሮችን መቆጣጠር ነው” በማለት በአቶ ቡልቻ በኩል የተነገረው ተሃድሦ የሚያሻው አስተሣሠብ ሲሆን ግን ደግሞ በገዢው ፓርቲ በኩልም ሊታረም የሚገባው ዓቢይ ነጥብ ያለ መስሎ ይሠማኛል፡፡

የህዝቦች ራሥን በራሥ የማስተዳደር ጥያቄ የመለሠው ሥርአት፣ በመረጡት መሪያቸው መተዳደርን መሠረት ያደረገው፣ በገቢያቸው የመተዳደር ስልጣንን ያጎናፀፈው ሥርዓት፣ የዴሞክራሢና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችም ሩቅ ሳይሄዱ፣ ማዕከላዊነት ላይ ሳያንጋጥጡ፣ ሳይጉላሉ በታችኛው የአሥተዳደር እርከን እንዲመለሡ ለማድረግ ያስቻለ የመሆኑ ጉዳይ ባለፈው ዓመት መጠናከር ሢገባው ወደኋላ የተመለሠበት እና በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በቀበሌና በክፍለ ከተማ ካድሬዎች የተቀሸቡበት አጋጣሚ መፈጠሩ የሚያሣስብና ገዢውን ፓርቲ ለበለጠ የቤት ሥራ የዳረገ መሥሎ ታይቶኛል፡፡ ከተቃዋሚ ፖለቲካውና መስመርተኛው ተሃድሶ ጋር ተያይዞ የቀበሌ ካድሬዎችን እና የክፍለ ከተማ ካድሬዎችን ተሃድሶም በበኩሌ በጣሙን ለአዲሱ ዓመት እመኛለሁ፡፡

ከአቶ ቡልቻ ተስፋና ምኞት የደነቀኝ ደግሞ “የሃገራችን ህዝቦች ኢትዮጵያ በእነርሡ እጅ እንዳለች ማወቅ ይኖርባቸዋል” የሚለው ነው፡፡ ለምን ቢሉ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት በፀደቀ ማግስት የዴሞክራሲ ተቋማትን ከማቋቋም እና ማደራጀት ጀምሮ በሠላም በዴሞክራሲና በልማት መስኮች በርካታ ቁልፍ ስራዎች ከመከናወናቸውም ባሻገር ኢትዮጵያ ከመለኮት ወይም ከአፈ ሙዝ ከሚመነጭ ስልጣንና አገዛዝ በመላቀቅ ስልጣን ከምርጫ የሚመነጭባትና እሣቸው አሁን ቢመኙትም የሃገራችን ህዝቦች ኢትዮጵያ በእነርሡ እጅ እንዳለች ያወቁበትና የሚያረቁበት ሥርዓት ከተፈጠረ በርከት ያሉ ዓመታትን ማስቆጠራቸው ነው፡፡

አቶ ቡልቻ ከኢህአዴግ በፊት በነበረችው ኢትዮጵያ ለይስሙላ ከሠፈሩት የህገ መንግስት ድንጋጌዎች በላይ መሪዎቹ እንዳሻቸው የሚሆኑበትና የህግ የበላይነት መርሆ ፈጽሞ ያልዞረባቸው

እንደ ነበሩ እንደማይዘነጉት ይታወቃል፡፡ በዛ ጊዜ የነበሩት መሪዎች ቃላቸው ህግ፣ ስሜታቸው ሥርዓት የሆነበት በየደረጃው ያሉ ባለሥልጣናትም በክቡር የሠው ህይወት ሣይቀር የሚወስኑበት ስርዓትም እንደነበር አይዘነጉትም፡፡ ይኼ ደግሞ በነበር የቀረ ነው፡፡ አሁን ሥርዓቱ በርግጥም የህዝብ ነው፡፡ ህዝቡም ኢትዮጵያ በእጁ ላይ እንዳለች ያውቀዋል፡፡ ህገመንግስቱም አረጋግጦለታል፡፡

ስለሆነም የተቃውሞው ፖለቲካ እና መስመርተኞችን ተሃድሦ በዚህ ዓመት እንሻለን፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ የተቃውሞው ፖለቲካ ኢህአዴግን መሸርደድ ሲያሻው የራሡን ባለማየትና በክፍል አንድ መጣጥፌ እንደተገለፀው የሃገራችንን ተምሣሌቶች ይናገረዋል እንጂ አይተገብረውም እንዳልኩት "ዝንጀሮ የራሷን -----" እንዲሉ ዓይነት አካሄድ ይሄዳል፡፡

ይህ አቅጣጫም በአንድነቱ አቶ አሥራት ጣሤ የአዲሡ ዓመት ምኞትና ተስፋ ተገልጧል፡፡ ኢህአዴግን እንዲህ አሉት አቶ አሥራት “ፓርቲው ችግሮችን በሠከነ አእምሮ በሰጥቶ መቀበል ስልት መፍታት እየተማነው ነው” ፡፡

ምርጫ 97 በአገራችን ታሪክ እጅግ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምርጫ ቢሆንም ተቃዋሚዎች ውጤቱን ለመቀበል ዝግጁ እንዳልነበሩ እናስታውሳለን፡፡ የውጪ ሃይሎችን ተንተርሠው ከምርጫ ሳጥን ያጡትን ሥልጣን በአመጽ ለማግኘት ያደረጉት ሙከራም የሚያስከትለውን ጉዳት ኢህአዴግ አስቀድሞ በመገመት እና በሠጥቶ መቀበል መርህ በመመራት ተቃዋሚዎች ወይም ዛሬ ኢህአዴግን ባልሰከነ መንገድ ችግሮችን ያያል የሚሉት እነ አቶ አሥራት ጣሤ ጉዳዩን በሠከነ መንገድ እንዲመለከቱት እና ከዚህ አካሄዳቸውም እንዲታቀቡ ለቀረበላቸው ጥሪ እምቢኝ አሻፈረኝ ማለታቸው የፈጠረውን ቀውስና በእነርሡ በራሳቸውም ላይ ያደረሠውን መፈረካከስም የሚረሣ ያለ አይመስለኝም፡፡ የሆነ ሆኖ ችግሩም በህግ መፍትሄ እንዲያገኝ ያደረገው ኢህአዴግ መሆኑን እና በዚህም ሂደት በአገራችን ስልጣን በህጋዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ እንደሚተላለፍ የተረጋገጠውም በዚሁ ሥርዓት መሆኑን ያሠመርንበት አጋጣሚ ነበር፡፡

ይሄ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መሥመር እነ አቶ አሥራት እንዳሉት አምባገነናዊ ሣይሆን በተለይ ባለፉት ሦስት ዓመታት መሥመሩን ይበልጥ መሬት የሚያሥነካ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አውጥቶ በመተዳደር ላይ የሚገኝ ሲሆን የእቅዱ ስኬቶችም መረጋገጥና በተግባር መታየት የጀመሩበት ባለፈው ዓመት ነው፡፡

መላ የአገራችን ህዝቦች በትክክለኛው የኢህአዴግ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መሥመር እየተመሩ አንፀባራቂ የልማት ድሎችን ማስመዝገባቸውን የቀጠሉበትን የባለፈውን ዓመት በአቶ አስራት መንገድ ማስታወስና ማሠብ ፍየል ወዲህ ቅዝምቅም ወዲያ እንደማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ነገሮችን ባስተውሎት እና በሥጥቶ መቀበል መርሆ በመገንዘብ በሚፈታው ኢህአዴግ መሪነት ከምርጫ 97 በኋላ የኪራይ ሠብሣቢነትን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በመናድ በገጠርና በከተማ የተካሄዱት እልህ አስጨራሽ ትግሎች በገጠር ከፍተኛ ውጤት እንዲመዘገብ በከተሞችም ችግሩ እየተዳከመ እንዲሄድ ያስቻለ ሢሆን፣ የአገራችን ህዳሴ የተበሠረበት ይህ ዘመን በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመርተኛው ኢህአዴግ ቀጣይነት ያለው ትግበራ እየጎለበተ መሄዱ ሲረጋገጥ እነ አቶ አሥራት ያመጡት መፍትሄና የአዲሡ ዓመት ምኞት በ97 የተሞከረውንና የከሸፈውን "የሚሊዮኖችን ድምፅ ለነፃነት " የቀለም አብዮት ነው፡፡ ስለሆነም ይህም አይሣካምና ይልቁንም በአዲሡ ዓመት ለተቃውሞው ፖለቲካ እና መስመርተኞች ዴሞክራሲያዊ ተሃድሶ እንሻለን፣ እንመኛለንም፡፡

ወደ ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት ስናመራ ደግሞ ከእነ አቶ አስራት ተመሣሣይ ግን ደግሞ ከሽርደዳው ይልቅ ምጽድቅናው ከበዛ አጀንዳቸው ጋር እንጋጫለን፡፡

በሠላማዊ ሠልፍ ስም ለሁከት የተጠራው የሠማያዊ ፓርቲ ሠልፍ በአክራሪ ሃይሎች ስለመጠለፉና በዚህችም ጭብጨባ የሠከሩት ኢንጅነሩ ሌሎቹን ፓርቲዎች "ፓርቲ አይደሉም" ሢሉ ላወረዱባቸው ልምጭ የተወረወረባቸውን የአፀፋ ምላሽና ጦር ለምናስታውሠው ሠዎች ኢንጅነሩ ያለፈውን ዓመት "በተፎካካሪ ፓርቲዎች አካባቢ መናበብና ወደውጤት ለመሄድ መንገድ የተጀመረበት ዓመት" ማለታቸው በርግጥም እኚህ ሠዎች ተሃድሦ ያሥፈልጋቸዋልና ምኞታችን የግድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይልቁንሥ ባለፈው ዓመት የተቃውሞውን ፖለቲካ በተመለከተ ያስተዋልነው ነገር መተባበርና መናበብን ሣይሆን የዚህን ተቃራኒ እንደሆነ አንዘነጋም፡፡ ሊያውም በተፎካካሪ ፓርቲዎች እንኳ እኮ አይደለም፣ በአንድ ፓርቲ ውስጥ፡፡ የመድረኩን እና የመድረኩ አባል የሆነውን አንድነት እሠጥ አገባ፣ የመድረኩ አመራር አባላትን እና የአንድነት አባላትን አመራሮች እንካ ሠላንቲያ፣ የአንድነቱን አቶ አሥራት ጣሤና ዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳ፣ ከአንድነቱ የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ ኢንጅነር ዘለቀ ረዲ ጋር የነበረ ድንጋይ መወራወር ከፍ ሢልም እህኮ ከአንድነት፣ ህብረት ከአንድነት እና ሠማያዊ ፓርቲ ከመድረኩ ጋር የነበራቸውን ግብ ግብ እና ግርግር ባለፈው ዓመት የምናስታውሰው ሁሉ የኢንጅነር ይልቃል ጌትነትን መታበይና የምርጫ 97ን ጭብጨባ ጦስ ለመድገም መንጠራወዝ ለተመለከትነው ሁሉ በርግጥም ለአዲሡ ዓመት ተሃድሷቸውን እንመኛለን፣ እንሻለን፡፡

መደምደሚያዬ ወደሆነው ወደ ዶ/ር ዳኛቸው አሠፋ አስተያየት ሣመራ ከላ በተመለከተው መሰረት ተቃዋሚዎቹ የካዱትን ያሳለፍነው ዓመት ሃቅ በተመለከተ እንዲህ ብለዋል፡፡ "በሃገራችን ከአንድ መሪ ወደሌላ መሪ የስልጣን ሽግግር በሠላም ተካሂዷል፡፡ ቢያንሥ እስካሁን ምንም የደም

መፍሠሥ የለም፡፡ የቀደመውን እንተወው ያለፈውን የኢትዮጵያ መቶ ዓመታት ታሪክ ብንመለከት በስልጣን ሽግግር ወቅት ሁልጊዜም ደም አለ፡፡

የተቃዋሚ ፓርቲዎች በራሣቸው ልዕልና መቆምና የራሣቸውን ሃሣብ ማፍለቅ ይኖርባቸዋል፡፡ አሜሪካ ከሚኖሩ ፖለቲከኞችም የቤት ሥራ መቀበል አይኖርባቸውም፣ የራሣቸው የፖለቲካ ማንነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አማራጭ የሆነ ሃሣብ ማቅረብ እንጂ ዝም ብለው ኢህአዴግም ሲሣሣት ኡኡ …ብለው መጮህ ብቻ አይደለም፤ አማራጭ የራሣቸውን ሃሣብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡" እውነቱ እንግዲህ ይህ የተቃዋሚዎች ቅጥረኝነት ነው፡፡ ስለሆነም በአዲሡ ዓመት የሚያሥፈልገን የተቃውሞው ፖለቲካ ህዳሤ ነው፡፡